# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## <u>የሽማግሌዎች ጥቆማ</u>

ዛሬም የሽማግሌዎች ጥቆማ ይቀጥላል። ባለፈው ሳምንት ያልጠቆማችሁ አባላት ዛሬ እንድትጠቁሙ በጌታ ፍቅር እንጠይቃለን። ምርጫው ደግሞ እንደ ጌታ ፍቃድ በሚቀጥለው ሳምንት ይከናወናል። ጌታ ይባርካችሁ።

## <u>የአርብ ፕሮግራም</u>

በአርብ **ፕሮግራም** እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በተለይም ደግሞ አሁን ወንድም ሲሳይ "የእግዚአብሔር መንግስት" በሚል ርእስ ተከታታይ ትምህርት በማስተማር ላይ ይገኛል። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፦ ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፦ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)

## <u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

# የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"እግዚአብሔርን አመስግኑ፥ ስሙን ጥሩ፤ ለአሕዛብ ሥራውን አውሩ።"
(1ዜና 16:8)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**December 9, 2018**

**ሕዳር 23፤ 2011 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................ | ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ |
| አምልኮ...................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም አያሌው አስፋው |
| ቃል ............. | ወንድም ዘሪሁን ዳዊት |
| ማጠቃለያ ................ | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

"ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ።"

(ኤፌ. 5:20)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ማክሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ምስጋና የድል መንገድ።

*"ምስጋና የሚሠዋ ያከብረኛል፤ የእግዚአብሔርን ማዳን ለእርሱ የማሳይበት መንገድ ከዚያ አለ።" (መዝ. 50፡23)*

ምስጋና እግዚአብሔርን የምናከብርበት መንገድ ነው። ምስጋናችን በፊቱ እንደሚያርግ መስዋዕት ለእግዚአብሔር የመአዛ ሽታ ነው። በምስጋና ውስጥ ደግሞ የደህንነት መንገድ አለ። እግዚአብሔርን ምስጋናን ለሚሰዋ ማዳኑን፣ ምህረቱን፣ እርዳታውን ይለግሳል። ምስጋና ዘርፈ ብዙ ነው፤ በዋናነት ግን ስናመሰግን ሶስት ነገሮችን እንዳደርጋለን።

(1) **ስናመሰግን እግዚአብሔር ላደረገልን ነገር እውቅና እየሰጠን ነው፡-** እግዚአብሔር ከቁጥር በላይ የሆነ ነገር አድርጎልናል። መዳናችን ቀዳሚ ነገር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር እኛ ሁላችን ሙታን ነበርን። ደግሞም በጨለማ ነበርን። ሕይወትን ያውም የዘላለም ሕይወት ስለሰጠን ሁልጊዜ ልናመሰግነው ይገባናል። በጨለማችንም ላይ ታላቅ ብረሃን በርቷል። መዳን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጆችም ሆነናል። ልጅነታችን ውስጥ ብዙ የከበረ ነገር አለ። ልጅነታችን ውስጥ የእግዚአብሔር አባትነት አለ፤ የእግዚአብሔር ፍቅር አለ፤ ወደ እርሱ አለመከልከል መቅረብ አለ እንዲሁም በእርሱ ደስታ ውስጥ መግባት አለ። ልጆች ብቻ ሳይሆን ያደረገን ደግሞም ለአገልግሎት ሾሞናል። በፊቱ ጉድ፣ ጉድ የምንል ባለማረጎች ተደርገናል። የክህነት ቅባት ፈሶብን፤ የክህነት ልብስ ለብሰናል። በምድር ሕይወታችንም ባርኮናል። ብዙ የምንቆጥራቸው በረከቶች አሉን። ታዲያ ይህንን ሁሉ ላደረገልን ጌታ ነብሳችን ማመስገን እና ውለታውን መቁጠር አለባት። ይህ እግዚአብሔርን ማክበር ነው።

(2) **ስናመሰግን የእምነት ቋንቋ እየተናገርን ነው፡-** በምስጋና ውስጥ እምነት አለ። የሚያመሰግን ሰው ከሁኔታዎች ሁሉ በላይ እግዚአብሔርን ከፍ ያደርጋል። አንዳንድ ጊዜ የምናልፍባቸው ሁኔታዎች ለማመስገን ላይመቹ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር ይመሰገናል። እማባቆም እንደተቀኘው የበረቱ ቦዶ መሆን፣ የእርሻው መጉደል ምስጋናንን መቀነስ የለበትም። በዚያም ውስጥ እርሱ ጌታ ነው። ጳሎስና ሲላስ በወህኒው የውስጠኛው ክፍል ምስጋና ሲሰው የእምነትን ቋንቋ እየተናገሩ ነበር። ከእስራቱና ከእንግልቱ እግዚአብሔር ይበልጣል እያሉ ነበር።

(3) **ስናመሰግን በጠላታችን ላይ መንፈሳዊ ውጊያ እየከፈትን ነው፡-** እግዚአብሔር ሲመሰገን ጠላት ይዋረዳል። ዳዊት እንደ ዘመረው ከአፋችን የሚወጣው ምስጋና ቂመኛ የሆነውን ጥላታችንን ዲያቢሎስን ይመታዋል። (መዝ.8፡2) ምስጋናና መንፈሳዊ ውጊያ ጎን ለጎን ናቸው። የእግዚአብሔር ህዝብ ምስጋና "በጉሮሮአቸው ነው፤ ሁለት አፍ ያለውም ሰይፍ በእጃቸው ነው።" (መዝ. 149፡ 6) ምስጋና ሲቀድም ጠላት ይመታል።

ወገኖቼ፡- ለእግዚአብሔር የምስጋናን መስዋእት እንሰዋ እንጂ ምስጋናን የምናጓድል አንሁን። ምስጋናችን እጁን ታንቀሳቅሳለች—ማዳኑን ታመጣለች።